ኅብረት ለምርጫ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

# የኅብረት ለምርጫ ምልከታ

## በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ሰራተኞች ምልመላ እና ስልጠና ጥራት

ሐምሌ 2015 ዓ.ም

# መግቢያ

በኢትዮጵያ ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም እና መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን፤ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤቶች ለአምስት ዓመታት የሚያገለግሉ የህዝብ ተወካዮች ተመርጠዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኢትዮጵያ ውስጥ ምርጫ እንዲያዘጋጅ ህጋዊ ስልጣን የተሰጠው ሲሆን፤ በምርጫ ሕጉ መሰረት ከምርጫ ቦርድ ስልጣን አንዱ የምርጫ ክልሎችን፣ የምርጫ ጣቢያዎችን እና የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ማቋቋም ነው። በዚህም መሰረት ለጠቅላላ የምርጫ ዑደት አስተማማኝነት ወሳኝ የሆኑ የመራጮች ምዝገባ፣ የዕጩዎች ምዝገባ፣ የድምጽ መስጫ ቀን አፈፃፀም እንዲሁም የድህረ- ምርጫ ሂደቶችን ያካተቱ የምርጫ ተግባራት የሚከናወኑት በእነዚሁ በሕግ በተቋቋሙ መዋቅሮች ነው። እነዚህ መዋቅሮች በመራጮች ምዝገባ፣ በእጩዎች ምዝገባ እና በድምጽ መስጫ ቀን አብዛኛውን የምርጫ ተግባራትን የማከናወን ኃላፊነት በተሰጣቸው የምርጫ አስፈፃሚዎች የተመሰረቱ ናቸው።

በኢትዮጵያ ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫን የማዘጋጀት ህጋዊ ግዴታውን ለመወጣት የምርጫ ቦርድ በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልል እና በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ደረጃ ከ150,000 በላይ የምርጫ አስፈፃሚዎችን መልምሎ፣ በማሰልጠን፣ አሰማርቷል።

ጎብረት ለምርጫ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ላይ ባደረገው ትዝብት እነዚህ የምርጫ አስፈፃሚዎች የምርጫ ሕጉ በሚያስቀምጠው መሰረት ምርጫን ለማስፈፀም የሚጠይቃቸው የቴክኒክ እና የስነምግባር አቅም ክፍተቶች እንደነበሩ ለማረጋገጥ ተችሏል። በአንዳንድ የምርጫ አስፈጻሚዎች የቴክኒክ እና የስነምግባር አቅም ማነስ ምክንያት ምርጫ ቦርድ በአንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች እና ምርጫ ክልሎች ውጤቱን ለመሰረዝ ተገዷል።

# በ6ተኛው ጠቅላላ ምርጫ የጎብረት ለምርጫ ትዝብት ግኝቶች

በ6ተኛው ጠቅላላ ምርጫ ትዝብት የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ፣ ጎብረት ለምርጫ የምርጫ ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚረዱ የተለያዩ የውትወታ እንቅስቃሴዎችን (Advocacy) ሲያደርግ ቆይቷል። የጎብረት ለምርጫ የትዝብት ሪፖርት በምርጫ አስፈጻሚዎች አቅም ላይ ከፍተኛ ሙያዊ ውስንነቶችን አመልክቷል። ለአብነት ያክል በድምጽ መስጫ ቀን በአንዳንድ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የማይለቅ የጣት ቀለም በመራጮች ጣት ላይ አለመደረጉ፣ በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው የሰፈሩ መራጮች ድምጽ እንዳይሰጡ የተከለከሉበት አጋጣሚዎች መኖራቸው እንዲሁም፣ በመራጮች መዝገብ ውስጥ ስማቸው የሌለ ዜጎችም ድምጽ እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው ሁኔታዎች ነበሩ።

በተጨማሪም በሶማሌ ክልል የገዥው ፓርቲ ባለስልጣናት የተሳሳተ የመራጮች ምዝገባ፣ ባዶ የመራጮች ምዝገባ ካርድ ማዘዋወር፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎች ናቸው የሚሏቸውን መራጮች ስም ማጥፋት፣ እንዲሁም በአብዛኛው "በመንግስት መዋቅር ውስጥ ተቀጣሪዎች ናቸው" ተብለው በሚታመኑት የምርጫ አስፈፃሚዎች በኩል የገለልተኝነት ጉድለት ተስተውሏል። ይህም ቦርዱ በክልሉ በመራጮች ምዝገባ ወቅት የተስተዋሉ ጉድለቶችን በማንሳት በክልሉ ምርጫ እንዲቋረጥ አድርጓል። ይህም ምርጫ ቦርድ በምርጫ አስፈፃሚነት የሚመለምላቸው ግለሰቦች ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት የጸዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት ጠንካራ ዘዴ እንዳልነበረው የሚያሳይ ነው።

ይህን ክፍተት መነሻ በማድረግ ጎብረት ለምርጫ በትዝብት ሪፖርቱ የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ አቅርቧል። ጎብረት ለምርጫ ያቀረበው ምክረ ሃሳብ ምርጫዎችን በሕግ መሰረት ለማስፈጸም የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ እና ስልጠና በድጋሚ እንዲከለስ የሚጠይቅ ነው። ጎብረት ለምርጫ በዚህ የምልከታ ጽሁፍ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ያሰማራቸውን የምርጫ አስፈፃሚዎች ለመመልመል እና ለማሰልጠን የተከተለውን ዘዴ እና ሂደት ይዳስሳል። በተጨማሪም በቀጣይ የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃ፣ ፍትሃዊ እና ግልጽ እንዲሆኑ፤ ውጤቶቻቸውም በዜጎች ተዓማኒነትን እንዲያገኙ ቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ምልመላ እና ስልጠና ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ማስተካከል ይኖርበታል።

# የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላ

የምርጫ ቦርድ ለመራጮች ምዝገባ እና ለድምጽ መስጫ ቀን 49,407 የምርጫ ጣቢያዎችን እንደሚያቋቁም የገለፀ ሲሆን፣ በእነዚህ የምርጫ ጣቢያ የምርጫ ሂደቱን የሚያሳልጡ እስከ 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) የምርጫ አስፈጻሚዎችን የበይነ መረብ የምልመላ ዘዴን በመጠቀም ለመመልመል አቅዶ ነበር።[1] ሆኖም ግን በተግባር 42,585 የምርጫ

1 National Electoral Board of Ethiopia (NEBE). "Observer Registration Form for the 6th General Elections." NEBE, 2021. Accessed June 26, 2023. https://www.nebe.org.et/wp-content/uploads/2021/05/Observer-Registration-Form-for-the-6th-General-Elections-2021.pdf.

ጣቢያዎች ለመራጮች ምዝገባ የተከፈቱ ሲሆን 40,365 የምርጫ ጣቢያዎች ለድምጽ መስጫ ቀን ተቋቁመዋል። በአጠቃላይ 152,700 የምርጫ አስፈፃሚዎች የመራጮች ምዝገባውን ማካሄድ ችለዋል።[2]

ለምርጫ አስፈፃሚነት ምርጫ ቦርዱ የትምህርት፣ የሥራ እና የገለልተኛነት ቅድመ -ሁኔታዎችን አስቀምጦ ነበር። አመልካቾች በማመልከቻቸው ላይ ከዚህ ቀደም በማንኛውም አይነት የታችኛው የመንግስት መዋቅር ውስጥ አለመስራታቸውን እና ቀድመው በተደረጉ ምርጫዎች (ከሲዳማ ሕዝበ-ውሳኔ ውጪ) በምርጫ አስፈፃሚነት አለመሳተፋቸውን እንዲያረጋግጡ ጠይቋል። እነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች የተቀመጡት የምርጫ አስፈፃሚዎችን ገለልተኛነት እና ሙያዊ ብቃት ለማረጋገጥ ሲሆን ማንኛውንም አይነት የውሸት መረጃ በማመልከቻ ውስጥ ማካተት የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል ተጠቅሷል።

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ ሂደት የሰለጠኑ ባለሞያዎች እጥረት፣ በተማረው የሕብረተሰብ ክፍል የታየው ደካማ የበጎ ፈቃድ ባህል እና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ ማነስ የተነሳ ፍቃደኛ እና ገለልተኛ የሆኑ የምርጫ አስፈፃሚዎችን የመመልመል ሂደቱ እጅግ ፈታኝ እንደነበር ገልጿል።[3]

የምልመላ ሂደቱ በዋናነት በጎ-ፈቃደኛ የሆኑ የምርጫ አስፈፃሚዎችን በድረ-ገፅ (online) ማስታወቂያ በማውጣት መመልመልን ያካተተ ነበር። ሆኖም ግን ይህ ሂደት በባህሪያቸው 'የበጎ ፈቃድ አበል ተከፋይ' የሆኑ የብቃት እና የገለልተኝነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ለማግኘት አዳጋች አድርጎታል።[4] ማስታወቂያው ግልጽነትን ከማረጋገጥ አኳያ የሚያበረታታ ቢሆንም የራሱ ተግዳሮቶች ገጥመውት ነበር። ቦርዱ ምልመላውን ለማከናወን በዚህ ማስታወቂያ ብቻ ላይ በመመርኮዙ ምክንያት የቀረቡት ማመልከቻዎች ቁጥራቸው ዝቅተኛ ከመሆናቸውም በላይ ቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች ቅጥር ማስታወቂያን በተደጋጋሚ እንዲያወጣ አስገድደውታል። በተጨማሪም ፖለቲካ ፓርቲዎች ቦርዱ በክልል እና በንዑስ-ክልል ደረጃ ላይ ባሉ የምርጫ ሂደቶች ላይ ያለው ስልጣን ላይ ጥርጣሬ አድሮባቸው ነበር።[5]

ቦርዱ በዚህ አዳጋች ሁኔታ ውስጥ የመለመላቸው የምርጫ አስፈፃሚዎች ወጣት የዩኒቨርስቲ ምሩቃን

2 National Electoral Board of Ethiopia (NEBE). "Sixth General Elections Results." NEBE, 2021. Accessed September 16, 2022. https://www.nebe.org.et/wp-content/uploads/2021/07/Final-Report-English.pdf,
3 The June 21, 2021 Ethiopian Parliamentary Elections: A Comprehensive Report." National Democratic Institute, October 2021. Accessed June 26, 2023. https://www.ndi.org/sites/default/files/2021-10/LEOME_Report_of_the_June_21_Elections_Final_Final.pdf.
4 Clark, Alistair, and Toby S. James. "Electoral administration and the problem of poll worker recruitment: Who volunteers, and why?" Electoral Studies, vol. 79, February 2023, Article 102220. Accessed June 26, 2023. https://doi.org/10.1016/j.electstud.2022.102220.
5 Supra Note at 4, ibid


Photo: BBC





የነበሩ ሲሆን እነዚህ ምሩቃን የምርጫ አስፈፃሚነት ሥራውን ለማከናወን የተነሳሱት በበጎ-ፈቃደኛነት መርህ ሳይሆን ለአጭር የኢኮኖሚ ጥቅም ነበር። በዚህም ምክንያት የመራጮች ምዝገባን ሂደትን እንዲያስፈጽሙ ኃላፊነት የተጣለባቸው አንዳንድ የምርጫ አስፈፃሚዎች “ክፍያችን በወቅቱ ስላልተፈፀመልን የምዝገባ ጣቢያዎችን አንከፍትም” ማለታቸው ይታወሳል። በተጨማሪም ከነዚህ አስፈጻሚዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ሌሎች የቦርዱን የብቃት ቅድመ-ሁኔታዎችን ቢያሟሉም ገለልተኛነታቸው ጥያቄ ውስጥ የገባ ነበር።

# ምክረ-ሃሳቦች

በማንኛውም የምርጫ ሂደት ውስጥ ጠንካራ የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ ሥነ-ሥርዓት ማበጀት አስፈላጊ ነው። የምርጫ አስፈፃሚዎች በእያንዳንዱ የምርጫ አስተዳደር መዋቅር ላይ የሚጫወቱትን ላቅ ያለ ሚና ታሳቢ በማድረግ የምልመላ ሥርዓቱ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ገለልተኛነት፣ ነፃነት እና ሙያዊ አቅም ሊያረግጥ ይገባል። ቦርዱ ሴቶች በምርጫ አስፈፃሚነት እንዲሰማሩ የወሰዳቸው እርምጃዎች የሚደነቁ ቢሆንም የምርጫ አስፈፃሚዎችን አቅም እና ገለልተኛነት ከማረጋገጥ አኳያ ጉልህ ክፍተቶች ተስተውለዋል። እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት፤

- የምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ምልመላ ለማከናወን ከአንድ በላይ ስልት መከተል ይኖርበታል። ይህም ማለት የምልመላ ማስታወቂያውን ለበርካቶች ተደራሽ ለማድረግ በተለያዩ የማስታወቂያ መንገዶች እና አገር በቀል ከሆኑ ድርጅቶች በማከናወን በቂ ቁጥር ያላቸውን የምርጫ አስፈፃሚዎች በተፈላጊው ሙያዊ እና ሥነ-ምግባራዊ የብቃት ደረጃ ለማግኘት ያስችለዋል።
- ቦርዱ የሲቪል ማህበራት፣ የብዙሃን ማህበራት፣ የሙያ ማህበራት እና ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸውን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በምልመላ ሂደቱ ውስጥ በስፋት በማሳተፍ ሙያዊ እና የሥነ-ምግባር መስፈርቶችን የሚያሟሉ የምርጫ አስፈፃሚዎችን በቀጣይ ምርጫዎች እንዲመለምል ያስችለዋል።
- በአጠቃላይ ቦርዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኛነት እና ሙያዊ አቅምን የማጐልበት አስፈላጊነት ታሳቢ በማድረግ በቀጣይ ምርጫዎች ጠንካራ የምልመላ ስርዓትን ለመዘርጋት ተግባራዊ ዕርምጃዎችን በመውሰድ አለበት።

# የምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና

ምርጫ ቦርድ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም እና መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም የተካሄደውን ምርጫ ለማስፈጸም ለተቀጠሩ የምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች የተሰጠው ስልጠና የተዋረድ የስልጠና ዘዴን (Cascading training Model) እንደተጠቀመ ከምርጫ ቦርድ ስልጠና ክፍል የተሰበሰበ መረጃ ያሳያል። ይህ ዘዴ በአጠቃላይ የሥልጠና እቅድ መንደፍ፣ የስልጠና ሰነዶችን ማዘጋጀት እና ማሳተም እንዲሁም 220 ዋና አሰልጣኞችን (Master trainers) መልምሎ ማሰልጠንን ያካትታል። ዋና አሰልጣኞች በምርጫ ማስፈጸም ርዕሰ ጉዳይ የተሻለ ዕውቀት ያላቸው ከምርጫ ቦርድ የውስጥ ሰራተኞች እና ከተለያዩ አጋሮች የተውጣጡ ነበሩ። በእነዚህ ዋና ሰልጠኞች በ21 የስልጠና ማዕከሎች የሰለጡ ከ5000 በላይ የመስክ አሰልጣኞች የነበሩ ሲሆን እነዚህ የመስክ አሰልጣኞች በ674 የስልጠና ማዕከሎች ለምርጫ አስፈፃሚዎች ለተሰጡ ስልጠናዎች የመምራት እና የማስተባበር ኃላፊነት ነበረባቸው። በቦርዱ የስልጠና ክፍል እንደተገለጸው የስልጠና ሂድቱ የምዝገባ እንዲሁም የድምጽ መስጫ ሂደቶችን ተግባራዊ በሆነ ልምምድ በማሳየት የምርጫ ቁሳቁሶችን ለአስፈፃሚዎች በማሳየት ተግባራዊ ዕውቀትን ለማስጨበት ያለመ ነበር።

ምርጫ ቦርድ የሠልጣኞችን አቅም ለማሳደግ ሁለት የሥልጠና መመሪያዎችን (የድምፅ ቀን መመሪያ እና የመራጮች ምዝገባ መመሪያ) በመንደፍ ተጠቅሟል። ይህም ሰልጣኞች (በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች) በየምርጫ ጣቢያዎች በመገኘት እያንዳንዱን የምርጫ ሂደት እንዲያስተባብሩ ለማድረግ ነው። መመሪያዎቹ ከምርጫ ቀን በፊት እና በድምጽ መስጫ ቀን ሊከሰቱ የሚችሉ ጉልህ ክስተቶችን ያስረዳሉ። እነዚህ መመሪያዎች የተዘጋጁት እንደ ሞዴል ማሳያ ቢሆንም በውስጣቸው ሰፊ ይዘት ያላቸው ነበር። በዚህም ምክንያት የምርጫ አስፈፃሚዎች የመመሪያዎቹን ይዘት ለመረዳትና ከራሳቸው ጋር ለማዋሃድ ፈታኝ ሆኖባቸው ነበር። ይህን ችግር ከግንዛቤ ውስጥ በመክተት እና ለመቅረፍ ምርጫ አስፈፃሚዎች የመመሪያዎቹን ሂደቶች በቀላሉ እንዲረዱቸው ቦርዱ አጭር የቪዲዮ ቅጂ አዘጋጅቷል።

የተዋረድ የሥልጠና ዘዴ (Cascading training Model) ሦስት የተለያዩ የአፈፃጸም ደረጃ እና የተለያዩ አሰልጣኞች ያሏቸው የሥልጠና ደረጃዎችን ያካትታል። ይህን ዘዴ በመከተል ቦርዱ በታችኛው ደረጃ ያሉ ስልጠናዎችን እንዲሰጡ የተጠቀማቸው አሰልጣኞች በዋና አሰልጣኞች የተሰጣቸውን ስልጠና በአግባቡ እንዳልተገነዘቡት ተስተውሏል። ይህም የሆነበት ምክንያት የተዋረድ ማሰልጠኛ ዘዴ በጥቅም ላይ በሚውልበት ወቅት ከአንድ ስልጠና ደረጃ ወደሌላ የስልጠና ደረጃ የሚተላለፉ መልዕክቶች በመሃል በተፈለገው መጠን እና ጥራት መተላለፍ ባለመቻላቸው ምክንያት ነው። በዚህ የስልጠና ዘዴ ሊተላለፉ የታቀዱ መልእክቶች ተቀይረው፣ ውጤታቸውም በተሳሳተ መልኩ ለሚወጥለው የስልጠና ወሳጆች ተላልፈው ቀድሞ ከታሰበው መልዕክት (original message) በተለየ መተላለፋቸው ነው። ከዚህም በላይ ለአሰልጣኞች ስልጠና እና ለተዋረድ ሥልጠናዎች (Cascading trainings) ሁለት የሥልጠና ቀናት ብቻ የተመደቡ ሲሆን ይህም ሥልጠናዎቹ ከሚሸፍኗቸው የስልጠና ርዕሶች እና ጭብጦች ስፋት አኳያ በቂ አልነበሩም። ሌላው ተግዳሮት ከስልጠናዎች ዝግጅት ጋር የተገናኘ ነው። ቦርድ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ስልጠናዎችን በተመሳሳይ ጊዜ ሰጥቷል። ስልጠናዎቹን ለመውሰድ የተመዘገቡት ሰልጣኞች ብዛት ሰፊ በመሆኑ እንዲሁም በማዕከል የምርጫ ቦርድ መቀመጫ እና በስልጠና ማዕከላት መካከል ባለው ርቀት ምክንያት ቦርዱ የስልጠናውን ውጤታማነት ከመቆጣጠር አኳያ ተግዳሮቶች እንዲያጋጥሙት አድርጎታል። የቅድሚያ ክፍያ እስካልተፈፀመ ድረስ ሰልጣኞች በስልጠና ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆን ሌላው የስልጠናውን የጊዜ ገደብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ እንቅፋት ነበር።[6]

ስልጠናው የሚሰጥበት ቋንቋን በተመለከተ ምርጫ ቦርድ አራት የተለያዩ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎችን (አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ አፋርኛ እና ሶማሊኛ) በመጠቀም ስልጠናውን ለመስጠት አቅዶ ነበር። ሆኖም ምርጫ ቦርድ አፋርኛ እና ሶማሊኛ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ዋና አሰልጣኞችን ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖበት ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ትክክለኛ ተነሳሽነት እና ልምድ ያላቸው ብቁ አሰልጣኞችን ለማግኘት እንደተቸገረ ቦርዱ ለኅብረት ለምርጫ የሰጠው መረጃ ያስረዳል። የፀጥታ ስጋት እና የትራንስፖርት እጥረት ባለባቸው ቦታዎች ስልጠናኦውችን ለማከናወን እክል የፈጠረ ሲሆን፣ በእነዚህ ቦታዎች ላይ አሰልጣኞች ለማሰልጠን ፈቃደኛ አልነበሩም። የስልጠና ቆሳቁሶችን በተለያዩ ሀገር በቀል ቋንቋዎች ቢዘጋጁም በትርጉም ስህተቶች ምክንያት የስልጠና ቁሳቁሶችን ጥራት ቀንሷል። በተጨማሪም በሥልጠና ማኑዋሎች ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው የአሠራር፣ የምርጫ ሂደቶችና የሕግ ማዕቀፎች ወቅታዊና ዝርዝር መረጃ አለማግኘት የሥልጠና ማኑዋሎችን ጥራት ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል።

## ምክረ-ሃሳቦች

በዚህ አስተያየት ላይ እንደተገለጸው የምርጫ ሂደቶች ያለችግር እንዲካሄዱ የምርጫ አስፈፃሚዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። ከዚህም በላይ ስለ ተግባራቸው ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እንዲሁም ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን መረጃዎችና ብቁነት

6 National Electoral Board of Ethiopia. (n.d.). Observers Accreditation. Retrieved July 4, 2023, from https://nebe.org.et/index.php/en/node/407

እንዲኖራቸው ተገቢውን ሥልጠና መስጠት ወሳኝ ነው። ስልጠናውን ለመጨረስ ሁለት ቀናት ብቻ የሚዘልቅ መሆኑን ምርጫ ቦርድ አስታውቋል። ይህ የምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠናውን በአግባቡ እንዳይረዱ እንቅፋት ይፈጥራል።

- በምርጫዎች ላይ የረዥም ጊዜ ተፅእኖ መፍጠር እንዲያስችል፣ ምርጫ ቦርድ ለስልጠና እና ለምርጫ ሰነዶች ዝግጅት ተጨማሪ ጊዜ መስጠት አለበት። በተጨማሪም ሰልጣኞችን በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል የተጨናነቀ የስልጠና ሂደት እንዳይኖር እና ስልጠናውን ያለችግር እንዲሰጡ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ቦርዱ ተግባራዊ ያደረገውን የስልጠና ሂደት በመከለስ የምርጫ አስፈፃሚዎች ኃላፊነቶቻቸውን በብቃት እና በገለልተኛነት እንዲወጡ ሊያደርግ ይገባል። ይህ ለስልጠና የሚሰጠውን ጊዜ ማርዘምን፣ ስልጠናዎችን አነስተኛ ለሆኑ ቡድኖች መስጠትን እንዲሁም ከተዋረድ የስልጠና ዘዴ ውጪ ያሉ ስልቶችን መቃኘትን ያካትታል። ይህን በማድረግ ምርጫዎች ተዓማኒ በሆነ መልኩ እንዲፈጸሙ እና የምርጫ አስፈፃሚዎች በሚገባ እንዲዘጋጁ ያግዛል።

በ6ተኛው ጠቅላላ ምርጫ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም(NDI) የኅብረት ለምርጫን  የዜጎች ምርጫ ትዝብት ተግባራትን የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይህ የምልከታ-ሃሳብ ታትሞ ሊወጣ የቻለው እና የታተመው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (USAID) በኩል ከአሜሪካ ሕዝብ በተበረከተ ቸር እገዛ ሲሆን ይዘቱ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ) ኃላፊነት እንጂ የUSAID፣ የአሜሪካ መንግስት አመለካከት የሚያንፀባርቁ አይደሉም።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ) በኢትዮጵያ የምርጫ ማሻሻያ እንዲኖር የተለያዩ ምልከታዎችን እንደ ጠቃሚ ግብአት ያዘጋጃል። ምልከታዎቹ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ እና በፖሊሲ ላይ ያተኮሩ ትንተናዎችን እንዲሁም የህግ ማዕቀፎችን እንዲሻሻሉ ልዩ ምክሮችን ይሰጣሉ። የኅብረት ለምርጫ ምልከታዎች የምርጫ ሥርዓት ግልጽ፣ ተጠያቂነት ያለው እና ሁሉን አቀፍ እንዲሆን የሚያስችል ንድፍ ሲያቀርቡ ይህም ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የኢትዮጵያን ዲሞክራሲያዊ ሂደቶች ለማጠናከር ለሚተጉ አካላት ሁሉ እንደ ግብአት እንዲያገለግሉ ያደርጋቸዋል።

## የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

ስድስት ኪሎ፣ ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢኒስቲቲውት ሕንፃ 2ኛ ወለል
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

+251 11 811 1455
www.cecoe.org
info@cecoe.org
twitter: @cecoeEth
facebook: CECOE21